የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
**Ministry of Trade**

ቀን 0 9 መጋቢት 2008
Date

ቁጥር 01-89/2624
Ref. No.

ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

በየደረጃው ታይቶ ማስተካከያ የተደረገበት የውህደት መመሪያ እንዲፀድቅላችሁ የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም. በቁጥር 15-3/89/1246/08 በተጻፈ ደብዳቤ መጠየቃችሁ ይታወሳል። በዚሁ መሰረት የፀደቀውን የውህደት መመሪያ 1 ጥራዝ በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት የተላከላችሁ መሆኑን አስታውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ያዕቆብ ያላ
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ</u>

- ለክቡር የንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ
- ለክቡር የንግድ አሰራርና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ
- ለሚኒስትር ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር
  <u>ንግድ ሚኒስቴር</u>

☎ +251-11-551 80 25-29
✉ 704
Fax +251-11-551 54 11
+251-11-553 1027
+251-11-552 2419
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# በኢ.ፌዴሪ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን

# የውህደት መመሪያ

**ቁጥር 550/2013**

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

# የውህደት መመሪያ ቁጥር 550/2013

መ ግ ቢ ያ

የንግድ ሥራ ሀገሪቱ በምትከተለው የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መርህ መሰረት ተገቢውን ስርዓት ተከትሎ መሄድ ያለበት በመሆኑ፤

በነጻ ገበያ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ፍትሀዊ የንግድ ውድድር የኢኮኖሚ ልማትን ለማፊጠን፤ የሸማቾችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እና የንግዱን ማህበረሰብ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስለሆነ፤

ቁጥጥር የማይደረግበት ውህደት የንግድ ውድድሩን፤ የህዝብ ጥቅም እና ገበያውን የሚያዛባና የሚጎዳ በመሆኑ፤

የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ውህደትን ለመቆጣጠር በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን ለመወጣት የሚያስችል መመሪያ ባለመኖሩ ምክንያት በአፈጻጸም እና በአሰራር ላይ ክፍተት በመፈጠሩ፤ የውህደት ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

ይህ መመሪያ በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 46(2) መሰረት ተደንግጓዋል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የውህደት መመሪያ ቁጥር 550/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

2.1. "ባለሥልጣን" ማለት የኢ.ፌ.ድ.ሪ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ነው፤

2.2. "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የኢ.ፌ.ድ.ሪ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ነው፤



Ministry of Trade Archives

2.3. “ምክትል ዋና ዳይሬክተር” ማለት የኢ.ፌ.ድ.ሪ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ውህደት ዳይሬክቶሬት የሚገኝበት ዘርፍ የሚመራ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ማለት ነው፤

2.4. “ዳይሬክተር” ማለት በኢ.ፌ.ድ.ሪ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የውህደት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ነው፤

2.5. “አዋጅ” ማለት የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ማለት ነው፤

2.6. “የንግድ ስራ” ማለት የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 2 (6) የተሰጠው ትርጓሜ ማለት ነው፤

2.7. “የንግድ ማህበራት ማለት” በንግድ ህግ አንቀጽ 210 የተሰጠው ትርጓሜ ማለት ነው

2.8. “ነጋዴ” ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 (5) የተሰጠው ትርጓሜ ማለት ነው፤

2.9. “የንግድ መደብር” ማለት በንግድ ህግ አንቀጽ 124 የተሰጠው ትርጓሜ ማለት ነው፤

2.10. “የውህደት ማስታወቂያ” ማለት ለመዋሀድ ዕቅድ ያላቸው ወገኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው የሚያቀርቡት ማመልከቻ ማለት ነው፤

2.11. “የውህደት ዳሰሳ ጥናት” ማለት ውህደት ለመፍቀድ ወይም ለመከልከል ወይም ለመሰረዝ በንግድ ውድድሩ ላይ ያስከተለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው ወይም እንደሌለው ለማጣራት የሚከናወን ተግባር ነው፤

## 3. ዓ ላ ማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

3.1. ውህደት በንግድ ውድድር፤ በገበያ እና በህዝብ ጥቅም ላይ የሚያስከትለውን የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ መከላከል፤

3.2. በአዋጁ መሰረት የሚታዩ የውህደት ደርጊቶችን ለማስተናገድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

የዚህ መመሪያ ወሰን በአዋጁ አንቀፅ 4 የተቀመጠው የተፈጻሚነት ወሰን ነው፡፡



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade

## ክፍል ሁለት
## የውህደት ትርጉም እና የውህደት ዓይነቶች

### 5. የውህደት ትርጉም

ውህደት ማለት በአዋጁ አንቀጽ 9(3) እንደተደነገገው ግላዊ ተቋምነታቸውን ይዘው ይኖሩ የነበሩ ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የንግድ ማህበራት ሲቀላቀሉ ወይም አንድ ዓላማ ያለው የንግድ ስራ ለማከናወን ሁሉንም ወይም ከፊሉን ሀብታቸውን ሲያቀላቅሉ ወይም በአንድ ሰው ወይም በብዙ ሰዎች በግዥ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሁኔታ የንግድ ማህበር አክስዮኖች፤ ሴኩሪቲዎች ወይም ንብረቶች የራስ ሲደረጉ ወይም የሌላ ሰው የንግድ መደብርን አመራር መቆጣጠር ሲቻል፤ የውህደት ድርጊት እንደተፈጸም ይቆጠራል፡፡

### 6. የውህደት ዓይነቶች- የኢኮኖሚ ሰንሰለትን መሰረት በማድረግ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የንግድ የኢኮኖሚ ሰንሰለትን መሰረት በማድረግ የውህደት ዓይነቶች የጎንዮሽ ዉህደት፤ከላይ ወደታች ዉህደት እና ጥርቅምቅም ዉህደት በማለት ይከፈላሉ፡፡

**ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል፡-**

**ሀ. <u>የጎንዮሽ ውህደት</u>፡-** ማለት በተመሳሳይ የገበያ እና መልክዓ ምድራዊ ክልል ዉስጥ በሚገኙ ተወዳዳሪ በሆኑ ወይም ሊሆኑ በሚችሉ በተመሳሳይ የማምረት ወይምየማከፋፈል ሰንሰለት ውስጥ በሚገኙ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚፈጠር የዉህደት አይነት ነው፡፡

**ለ. <u>ከላይ ወደታች ውህደት</u>፡-** ማለት በተለያየ ደረጃ የሚሰሩ ነጋዴዎች ሆነው ነገር ግን አንዱ ለአንዱ ግብአት ማሟያ ደረጃ ላይ የሚገኝ የምርት ሂደት ሰንሰለት ዉስጥ በሚገኙ መካከል የሚደረግ ውህደት ነው፡፡

**ሐ. <u>ጥርቅምቅም ውህደት</u>፡-** ማለት የተለያዩ የገበያ ምርትና አገልግሎት ውስጥ ባሉ አቅራቢዎች መካከል የሚደረግ ውህደት ነው፡፡የተለያዩ ነገር ግን ግንኙነት ያላቸው ምርቶችን በሚያመርቱ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠር ውህደት እና የማይገናኙ ምርቶችን በሚያመርቱ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠር ውህዶቶች በዚህ የውህደት ዓይነት ውስጥ ይካተታሉ፡፡



Ministry of Trade

## 7. የውህደት ዓይነቶች- ግብይትን መሰረት በማድረግ

7.1. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል የንግድ ድርጅቶች ወይም ማህበራት ወይም ግለሰቦች የሚፈጽሙትን የግብይት ዓይነት መሰረት በማድረግ ውህደት የአክሲዮን ባለቤትነት ፣የሀብት ባለቤትነት የድርጅቶች ጥምረት የሴኩሪቲ ባለቤትነት በመባል በአራት ይከፈላል፡፡

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል፡-

ሀ. የአክስዮን ባለቤትነትን ማለት፡- ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ግላዊ ተቋምነት ካላቸው ከራስ ወይም ሌሎች ድርጅቶች አክሲዮን በግዢ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ የአክሲዮን ባለቤትነት ሲኖራቸው ነው፡

ለ. የሀብት ባለቤትነት ማለት፡- ድርጅቶች ወይም ግለሰቦቸ ያላቸውን አንድ የተወሰነ ሃብት ለሌላ ድርጅት በሽያጭ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ሲያስተላልፉ ነው፡፡

ሐ. የድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጥምረት ማለት፡- የንግድ ማህበራት ወይም ግለሰቦች አንድ ዓላማ ያለው የንግድ ስራ ለማከናወን ሁሉንም ወይም ከፊሉን ሀብታቸውን ሲያቀላቅሉ የሚፈጥሩት ጥምረት ማለት ነው፡፡

መ. ሴኩሪቲ ማለት፡- ገንዘብ ነክ ያላቸው ሰነዶች ሆነው በግዢ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ የሚተላለፍ ሰነድ ነው፡፡

7.2. ከላይ በአንቀጽ 7.1. ስር የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ተቆጣጥሮ መያዝ፣ዓመታዊ የሽያጭ/ ሃብት፣ የገበያ ድርሻ ፣በገበያ ውስጥ የአቅራቢዎች ስብስብ መጠን እና አግባብነት ያለው ገበያ በውህደት ዳሰሳ ወቅት ከግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናሉ፡፡

ሀ. ተቆጣጥሮ መያዝ ማለት፡- አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ የሌላዉን ድርጅት ወይም ግለሰብ ከ50% በላይ ድርሻ ሲይዝ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ አብላጫ ድምፅ መስጠት ሲችል ወይም የቦርድ አባላትን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በአብላጫ ድምፅ መምረጥ የሚችልበትን ወይም ውሳኔያቸዉን በድምፅ መሻር የሚችልበትን



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives

ሁኔታ የሚፈጥር ወይም የድርጅቱን ፖሊሲ ላይ ተፅእኖ ማሳደር የሚችልበትን ሁኔታ የሚፈጥር ከሆነ ነው፡፡

**ለ. ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ ማለት፡-** ከማንኛውም የንግድ እቃ ወይም አገልግሎት ሽያጭ የተገኘ ውሳኔ ከሚሰጥበት አመት በፊት የነበረ የመጨረሻ አመት አጠቃላይ የሽያጭ ገቢ ሲሆን፤ የንግድ ድርጅቱ አዲስ ከሆነ እና የስራ ዘመኑ ከአንድ የበጀት አመት በታች ከሆነ በሰራባቸው ጊዜያት የተገኘ አጠቃላይ ገቢ ሆኖ ህጋዊ ፈቃድ ባለው የሂሳብ ወይም የኦዲተር ባለሙያ የተረጋገጠ ሰነድ ነው፡፡

**ሐ. የገበያ ድርሻ ማለት፡-** አግባብነት ባለው የገበያ ወይም የምርት ክልል ውስጥ አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ገቢን ወይም አቅምን ወይም የምርት ብዛትን መሰረት ያለው የገበያ ድርሻ የሚያሳይ ነው፡፡ የገበያ ድርሻ ለማስላትም የምርት ሽያጭ መጠን ወይም ካፒታል ወይም ሃብት ለአጠቃላይ በገበያው ውስጥ ያሉ የሌሎች ድርጅቶች ድምር መጠንን በማካፈል ይሰላል፡፡

**መ. በገበያ ውስጥ የአቅራቢዎች ስብስብ መጠን ማለት፡-** የአቅራቢዎች ስብስብ መጠን አግባብነት ባለው የገበያ ክልል ውስጥ ከፍተኛ የገበያ ድርሻ ያላቸው አቅራቢዎች ምን ያህል እንደሆኑና እነዚህ አቅራቢዎች ከአጠቃላይ ገበያው ወይም ኢንዱስትሪው ውስጥ ምን ያህል ድርሻ እንዳላቸው ለማየት የሚረዳ ነው፡፡ ይህንን ለመለካትም የስብስብ መጠን (Concentration Ratios) ወይም የHerfindahl-Hirschman Index ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆኑ በConcentration Ratios ከፍተኛ የገበያ ድርሻ ያላቸው ሦስት ወይም አራት ወይም አምስት ድርጅቶች በመውሰድ ውጤቱ ከ70% በላይ ከሆነ ወይም በHerfindahl-Hirschman Index ውጤቱ ከ25% በላይ ከሆነ ውድድር ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅኖ ሊኖረው እንደሚችል ያመላክታል፡፡

**ሠ. አግባብነት ያለውን ገበያ ማለት፡-** የምርት ወይም አገልግሎት እና ምርቱ የሚገኝበት አካባቢን የሚያካትት ሲሆን በውድድር ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ለመዳሰስ ይረዳል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የውህደት ማስታወቂያ ስለማቅረብ

8. ማንኛም ነጋዴ በውህደት ስምምነት ወይም ቅንብር ውስጥ ለመሳተፍ ሲያቅዱ የውህደት ማስታወቂያ በጽሁፍ ሆኖ በአመልካቾች በራሳቸው ወይም በህጋዊ ወኪሎቻቸው ሊቀርብ ይችላል፡፡

9. የማቅረቢያ ቋንቋ እና መንገዶች

9.1. የውህደት አመልካቾች ማስታወቂያቸውን ለባለስልጣኑ በአካል ወይም በፋክስ ወይም በኢሜል ወይም በፖስታ አመልካቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ማመልከቻቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

9.2. አመልካቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው የውህደት ማመልከቻቸውን እና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶችን በአማርኛ ቋንቋ ማቅረብ አለባቸው፡፡ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጁ ሰነዶች ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው መቅረብ አለባቸው፡፡

10. የውህደት ማስታወቂያ ይዘት እና ቅድመ ሆኔታዎች

10.1. የውህደት ማስታወቂያ የሚከተሉትን ይዘቶች ያካተተ መሆን አለበት እነሱም፤ ቀን፤የተዋሀጆች ስምና አድራሻ ፤የንግድ ስራ ቦታ፤ ያቀዱት የንግድ ስራ፤የውህደት ሁኔታ፤የካፒታል መጠን ፤የማስረጃዎች ዝርዝር የአመልካቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎች ፊርማ እና ማህተም ናቸው፡፡

10.2. የውህደት አመልካቾች የንግድ ማህበራት በሆኑ ጊዜ የታደሰ የንግድ ፈቃድ/ምዝገባ ፣ህጋዊ የመመስረቻ ጽሑፍ፣ ድርጅቶች መዋሃድ ስለመፈለጋቸው የሚገልጽ ተመላሽ ኦሪጅናል ወይም የተረጋገጥ ኦሪጅናል ኮፒ ቃለ ጉባኤ፣በሚሞላው ቅጽ ላይ የሚያርፍ የሚወሃዱት ድርጅቶች ማህተም ፣ህጋዊ ውክልና ማስረጃ ለውጭ አገር ድርጅቶች ወይም ከሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በጋራ በሚሰሩ የውጪ ዜጎች ከሆነ በወቅቱ ስራ ላይ ባለው የኢንቨስትመንት አዋጅ በተቀመጠው መስፈርት፤ በውጭ ድርጅቶች የሚቀርቡ ሰነዶችና ማስረጃዎች እንደ አግባብነቱ በንግድ ሚኒስቴር፤ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር፤ ወይም በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተረጋገጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ማንኛውም ድርጅት ማቅረብ የሚጠበቅበት የኦዲት ሪፖርት በሂሳብ አዋቂ ወይም



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

ኦዲተር የተረጋገጠ የኦዲት ሰነድ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችና ማስረጃዎች መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

10.3. የውህደት አመልካቾች ግለሰቦች ሆነው የአክሲዮን፣ ሴኩሪቲ ከንግድ ድርጅቶች ለመግዛት በሆነ ጊዜ ግለሰቡን የሚገልጽ የታደሰ የመኖሪያ መታወቂያ፤ፓስፖርት መግዛት የሚፈልገው የአክሲዮን፤ ንብረቶች ወይም ሴኩሪቲ መጠን በብር (በቃለ ጉባኤ ወይም በደብዳቤ የተደገፈ)፣ ህጋዊ ውክልና ማስረጃ፣ ለውጭ አገር አመልካች ከሆነ በወቅቱ ስራ ላይ ባለው የኢንቨስትመንት አዋጅ በተቀመጠው መስፈርት፡ ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችና ማስረጃዎች መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## ክፍል አራት
## የውህደት ዝቅተኛ ገደብ በጠቅላላው

### 11. የውህደት ዝቅተኛ ገደብ

11.1. ዝቅተኛ ገደብ ማለት በንግድ ውድድር፤ በገበያ እና በህዝብ ጥቅም ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖራቸው የሚችሉ የውህደት አይነቶች ለመለየት የሚያስችል ዝቅተኛ ገደብ ነው፡፡

11.2. ባለስልጣን መ/ቤቱ ውህደትን በሚመረምርበት ወቅት ዝቅተኛ ገደብን ለመወሰን የአመልካቾችን አመታዊ ሽያጭ፤ንብረት ወይም ያስመዘገቡትን ካፒታል ድምር መነሻ ሊያደርግ ይችላል፡፡

11.3. አመልካቾች ስለሚኖራቸው መነሻ ካፒታል በሌላ ህግ የተወሰነ ከሆነ በህጉ ላይ የተቀመጠው የካፒታል መጠን የዝቅተኛ ገደብ መነሻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡



ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዛግብት ቤት

12. በዚህ መመሪያ ውህደትን ለመቆጣጠር አላማ ውህደት ቀላል፤ መካከለኛ እና ከፍተኛ ተብሎ ሊመደብ ይችላል፡፡

13. ዓመታዊ ሽያጭ ወይም ንብረት ወይም ያስመዘገቡትን ካፒታል መጠናቸው ከ30,000,000.00 (ሰላሳ ሚሊዮን) የኢትዮጵያ ብር በታች ቀላል ውህደት በሚል የሚመደብ ሲሆን የካፒታል መጠናቸው ከ30,000,000.00 (ሰላሳ ሚሊዮን) እስከ 300,000,000.00 (ሶስት መቶ ሚሊዮን) የኢትዮጵያ ብር መካከለኛ ውህደት እንዲሁም ከ300,000,000.00 (ሶስት መቶ ሚሊዮን) የኢትዮጵያ ብር በላይ ያለው ውህደት ከፍተኛ ተብሎ ይወሰዳል፡፡

14. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 13 የተቀመጠ አመታዊ ሽያጭ ወይም ንብረት ወይም ያስመዘገቡትን ካፒታል መጠን ዝቅተኛ ገደብ መነሻው የውህደት አመልካቾች አመታዊ ሽያጭ ወይም ንብረት ወይም ያስመዘገቡትን ካፒታል መጠን ድምር ነው፡፡

15. ከዝቅተኛ ገደብ በላይ የሆኑ የውህደት አመልካቾች ለመዋሀድ ሲያቅዱ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለባቸው የዳሰሳ ጥናትም ይደረግባቸዋል፡፡

16. አመታዊ ሽያጭ ወይም ንብረት ወይም ያስመዘገቡትን ካፒታል መጠናቸው ከ30,000,000.00 (ሰላሳ ሚሊዮን) የኢትዮጵያ ብር በታች የሆኑ የውህደት ማስታወቂያዎች በተመለከተ ተዋሀጆች ባለስልጣኑን እንዲያሳውቁ በአዋጁ ቢቀመጥም ለባለስልጣኑ እንዳሳወቁ ተቆጥሮ ባሉበት የውህደት ፈቃድ ለመመዝገብ ስልጣን ላለው አካል ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ለዝቅተኛ ውህደት ማስታወቂያዎች የዳሰሳ ጥናት ስራዎች አይካሄድባቸውም፡፡ ነገር ግን ባለስልጣን መ/ቤቱ ውህደቱ በገበያ ላይ ያለውን ተጽእኖ ከመከታተል እና ከማጣራት አያግደውም፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል አምስት
## የውህደት ዳሰሳ ደረጃዎች

17. ጠ ቅ ላ ላ

1. በተዋሀጆች የቀረቡ ማስታወቂያዎች ሙሉ ማስታወቂያዎች የሚባሉት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዙ ከሆነ ነው፡፡ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ መነሻ ቀንም የሚቆጠረው መረጃዎቹ ተጠቃለው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ያለው ነው፡፡
2. ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ወደ ደረጃ ሁለት የሚተላለፍ ከሆኑ ባለስልጣኑ ይህንኑ ውሳኔ ለአመልካቾች መግለጽ ይኖርበታል፡፡
3. ባለስልጣኑ በአመልካቾች የቀረበው ማስታወቂያ ላይ ያለውን ምልከታ ከአመልካቾች በተጠየቀ ጊዜ ያሳውቃል፤ ውህደቱ በንግድ ውድድር፤ በገበያ እና በህዝብ ጥቅም ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ጎን በተመለከተ አመልካቾች ያላቸው ሌላ አማራጭ ካለ ይጠይቃል፡፡ የሚቀርበውን አማራጭም ያጠናል፡፡
4. በውህደት ዳሰሳ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውህደቱ በውድድር ላይ ሊያደርስ የሚችለው አዎንታዊና አሉታዊ ውጤት፤ውህደቱ ሊፈጥር የሚችለው ውጤታማነት፤ውህደቱ በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያለው ውጤት፤ውህደቱ ሌሎች ተወዳዳሪነትን ለማበረታታት የሚያስችሉ ውጤቶች ያሉት መሆኑ፤ውህደቱ የህዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑ የሚኖረው የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ ምን እንደሆነ በዝርዝርና በጥልቀት የሚመረመር ይሆናል፡፡
5. የስራው ፍሰቱን በሚመለከት ዋና ዳይሬክተሩ የቀረበው የውህደት ማስታወቂያ ለግንዛቤ ማሳደግና የህግ ተፈፃሚነት ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ይመራል፣ ም/ዋና ዳይሬክተሩም ለዳይሬክቶሬቱ ይመራል፣ ዳይሬክቶሬቱም እንዳስፈላጊነቱ የዳሰሳ ጥናት/ የሰነድ ፍተሸ በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ለዘርፉ ም/ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፣ ም/ዋና ዳይሬክተሩም በውሳኔ ሃሳቡ ላይ የራሱን አስተያየት አክሎበት ለዋና ዳይሬክተሩ ይመራል፣ ዋና ዳይሬክተሩም የውሳኔ ሃሳቡን በማረጋገጥ የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
ቤተ መዛግብት

## 18. መካከለኛ ውህደት

መካከለኛ ውህደት በሁለት የዳሰሳ ጥናት ደረጃዎች ውስጥ ሊያልፍ ይችላል፡፡

### 18.1. ደረጃ አንድ

1. የውህደት ማስታወቂያዎችን በክፍል ሦስት የተጠቀሱትን አግባብነት ያላቸው ቅደመ ሁኔታዎች አሟልተው እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡
2. መካከለኛ ውህደት ማስታወቂያ ተሟልቶ ከቀረበ በኃላ በ 15 የስራ ቀናት ውስጥ ታይቶ ውሳኔ የሚያገኝ ይሆናል፡፡ይህ የጊዜ ገደብ እንደአስፈላጊነቱ ማስታወቂያ ለማስነገር የሚወስደውን ጊዜ አይጨምርም፡፡
3. ባለስልጣኑ ከባለጉዳዮችና ከሶስተኛ ወገን አንጻር በዉህደቱ ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ውህደቱ የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ የማይኖረው ከሆነ ውህደቱን ይፈቅዳል፡፡
4. ውህደቱ በንግድ ውድድሩ፤ በህዝብ ጥቅም እና በገበያ ሁኔታ ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ሁኔታ ተገልጾ በቅድመ ሁኔታ ለመፍቀድ የሚቻል ከሆነ እና ቅድመ ሁኔታውን ተዋህጆች የሚያሟሉ ከሆነ ውህደቱ ይፈቀዳል፡፡
5. ባለሥልጣኑ ውሳኔ ለማስተላለፍ በቂ የሆነ መረጃ ካለ ወይም ተጨማሪ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ የማያስፈለግ ከሆነ በዚሁ ደረጃ ውስጥ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡
6. መካከለኛ የውህደት ማስታወቂያዎች ታይተው በ15 የስራ ቀናት ውሳኔ እንዳያገኙ ሊያደርጉ የሚችሉ ምክንያቶች ካሉ እና ለዚህም ተጨማሪ መረጃዎችን የሚያስፈልግ ከሆነ ጉዳዩ ወደ ደረጃ ሁለት በማስተላለፍ በባለስልጣን መ/ቤቱ በ10 ቀናት ይራዘማል፡፡
7. መካከለኛ የውህደት ማመልከቻዎች በዚህ ደረጃ ላይ ታይተው ውሳኔ የማያገኘው፡፡

    ሀ. ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገ፤

    ለ. ከገበያ፣ ከውድድርና ከህዝብ ጥቅም አንፃር ዳሰሳ ሲካሄድ የተገኘው ግኝት ለቀረበው ማስታወቂያ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በቂ ተጨማሪ ግዜና የውሳኔ ሃሳብ የሚያስፈልግ መሆኑ ከታመነበት፤

    ሐ. ሌሎች በውህደት ባለስልጣኑ እንደ አሳማኝ ምክንያቶች የሚታዩ ጉዳዮች ከቀረቡ ነው፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives

8. በደረጃ አንድ መካከለኛ የውህደት ማስታወቂያዎች ታይተው ውሳኔ ለመስጠት የማይቻል ሲሆን እና ጥልቀት ያለው ዝርዝር ዳሰሳ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በደረጃ ሁለት የሚታይ ይሆናል፡፡

18.2. **ደረጃ ሁለት**

1. በዚህ ደረጃ ባለሥልጣኑ የሚዋሃዱ አካላትን በጉዳዩ ዙሪያ የበለጠ መረጃ እንዲያቀርቡ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ወደዚህ ደረጃ የተላለፈው ጉዳይ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
3. ከዚህ በላይ በተካሄደው ዳሰሳ ጥናት ዉህደቱ በንግድ ዉድድር ከህዝብ ጥቅም እና በገበያ ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ እንደማይኖረዉ ካመነበት ዉህደቱን ይፈቅዳል፣
4. ዉህደቱ በንግድ ዉድድር ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚኖረዉ ካመነበት ዉህደቱን ይከለክላል፣
5. ዉህደቱ በንግድ ዉድደር ላይ ሊያስከትል የሚችለዉ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ የተወሰኑ ተያያዥ ግዴታዎች በማከል ዉህደቱን ሊፈቅድ ይችላል፡፡
6. ውህደቱ ከሚያስከትለው የጎላ አሉታዊ ተጽኦኖ ይልቅ ከቴክኖሎጂ፣ ከአሰራር ቅልጥፍና ወይም ከሌላ ተወዳዳሪነትን ከሚያጠናክር ጠቀሜታ አንጻር የሚያስገኘው ጥቅም የሚያመዝንና ይህም ጠቀሜታ ውህደቱ ከተከለከለ በሌላ መንገድ ሊገኝ የማይችል ሲሆን ባለስልጣኑ ውህደቱን ይፈቅዳል፡፡

19. **ትልልቅ ውህደት በተመለከተ**

19.1. **ደረጃ አንድ**

1. የውህደት ማስታወቂያ በክፍል ሦስት የተጠቀሱትን አግባብነት ያላቸው ቅደመ ሁኔታዎች አሟልተው እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡
2. ትልልቅ የውህደት ማስታወቂያ ተሟልቶ ከቀረበ በኋላ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ታይቶ ውሳኔ የሚያገኝ ይሆናል፡፡
3. ባለስልጣኑ ከባለጉዳዮችና ከሶስተኛ ወገን አንጻር በዉህደቱ ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ውህደቱ የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ የማይኖረው ከሆነ ውህደቱን ይፈቅዳል፡፡

Ministry of Trade Archives

4. ውህደቱ በንግድ ውድድሩ፤ በህዝብ ጥቅም እና በገበያ ሁኔታ ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ሁኔታ ተገልጾ በቅድመ ሁኔታ ለመፍቀድ የሚቻል ከሆነ እና ቅድመ ሁኔታውን ተዋሀጆች የሚያሟሉ ከሆነ ውህደቱ ይፈቀዳል፡፡
5. ባለሥልጣኑ ውሳኔ ለማስተላለፍ በቂ የሆነ መረጃ ካለ ወይም ተጨማሪ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ የማያስፈለግ ከሆነ በዚሁ ደረጃ ውስጥ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡
6. ትልልቅ የውህደት ማመልከቻዎች ታይተው በ30 የስራ ቀናት ውሳኔ እንዳያገኙ ሊያደርጉ የሚችሉ ምክንያቶች ካሉ እና ለዚህም ተጨማሪ መረጃዎችን የሚስፈልግ ከሆነ ጉዳዩ ወደ ደረጃ ሁለት በማስተላለፍ ለ15 የስራ ቀናት ይራዘማል፡፡
7. ትልልቅ የውህደት ማመልከቻዎች በዚህ ደረጃ ላይ ታይተው ውሳኔ የማያገኘው፡፡

   ሀ. ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገ፤

   ለ. ከገበያ፣ ከውድድርና ከህዝብ ጥቅም አንፃር ዳሰሳ ሲካሄድ የተገኘው ግኝትለቀረበው ማስታወቂያ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በቂ ተጨማሪ ጊዜና የውሳኔ ሃሳብ የሚያስፈልግ መሆኑ ከታመነበት፤

   ሐ. ሌሎች በውህደት ባለስልጣኑ እንደ አሳማኝ ምክንያቶች የሚታዩ ጉዳዮች ከቀረቡ ነው፡፡
8. በደረጃ አንድ ትልልቅ የውህደት ማስታወቂያዎች ታይተው ውሳኔ ለማግኘት የማይቻል ሲሆን እና ጥልቀት ያለው ዝርዝር የዳሰሳ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በደረጃ ሁለት የሚታይ ይሆናል፡፡

## 19.2. ደረጃ ሁለት

1. በዚህ ደረጃ ባለሥልጣኑ የሚዋሃዱ አካላትን በጉዳዩ ዙሪያ የበለጠ መረጃ እንዲያቀርቡ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ወደዚህ ደረጃ የተላለፈው ጉዳይ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
3. በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት ዉህደቱ በንግድ ዉድድር፤በገበያ እና በህዝብ ጥቅም ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ እንደማይኖረዉ ካመነበት ዉህደቱን ይፈቅዳል፣

ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዛግብት

4. ዉሀደቱ በንግድ ዉድድር ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚኖረዉ ካመነበት ዉሀደቱን ይከለክላል፣ ወይም
5. ዉሀደቱ በንግድ ዉድደር ላይ ሊያስከትል የሚችለዉ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ የተወሰኑ ተያያዥ ግዴታዎች በማከል ዉሀደቱን ሊፈቅድ ይችላል፡፡
6. ውሀደቱ ከሚያስከትለው የጎላ አሉታዊ ተጽኦኖ ይልቅ ከቴክኖሎጂ፤ ከአሰራር ቅልጥፍና ወይም ከሌላ ተወዳዳሪነትን ከሚያጠናክር ጠቀሜታ አንጻር የሚያስገኘው ጥቅም የሚያመዝንና ይህም ጠቀሜታ ውህደቱ ከተከለከለ በሌላ መንገድ ሊገኝ የማይችል ሲሆን ባለስልጣኑ ውህደቱን ይፈቅዳል

## ክፍል ስድስት
## የውህደት ማስታወቂያ ዳሰሳ ጥናት ስለማድረግ እና ውሳኔ መስጠት

### 20. ቅድመ ውህደት ዳሰሳ ጥናት ስለማካሄድ

የቅድመ ውህደት ዳሰሳ ጥናት ከንግድ ውድድር ፤ከገበያ ሁኔታ እና ከህዝብ ጥቅም አንጻር ይካሄዳል፡፡

20.1. የቅድመ ውህደት ዳሰሳ ጥናት ከንግድ ውድድር አንጻር ሲካሄድ የሚከተሉት ነጥቦች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡-

ሀ. በገበያ ውስጥ ያለው የገበያ ተዋናይ መጠን

ለ. ገበያውን በበላይነት ለመያዝ ያላቸው/የሚኖራቸው አቅም

ሐ. በተመሣሣይ የንግድ መስክ ገበያ ውስጥ ለመግባት የሚኖረው መሰናክል እና በገበያ ውስጥ ያሉትን ተወዳዳሪዎች ከገበያ ውጭ የማድረግ አቅም

መ. ምርቱን የሚተኩ የንግድ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች በገበያ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ወይም መጠን፣

ሠ. የውህደት ድርጊቱን የሚፈጸምበት የንግድ ስራ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የንግድ እቃዎች ወደ አገር በመግባት በኩል ያለው ደረጃ

ረ. በገበያው ውስጥ ያለው እድገት፣ ፈጠራ፣ ዋጋ እና ተፈጥሯዊ ባህሪ



Ministry of Trade Archives

ሰ. በገበያው ውስጥ ያሉ አቅራቢዎችን እና ሸማቾችን በማወክ በኩል ያለዉ ደረጃ እና በአቅራቢዎች፣አከፋፋዮች እና ቸርቻሪዎች የመደራደር አቅም ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር መሆኑ፣

ሸ. ሌሎች ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ የዳሰሳ ጥናቱን መደረግ ይኖርበታል፡፡

20.2. የቅድመ ውህደት ዳሰሳ ጥናት ከገበያ አንጻር ሲካሄድ የሚከተሉት ነጥቦች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡

ሀ. አግባብነት ያለው የገበያ ሁኔታ ትንተና

ለ. የምርት/አገልግሎት አቅርቦትና ፍላጎት ሁኔታ፡-

ሐ. የምርት/አገልግሎት ዋጋ፣ የጥራት ደረጃ፣

መ. የግብዓት ሁኔታ፣

ሠ. የምርት/አገልግሎት ስርጭት መስመር ሁኔታ፣

ረ. የገበያ ድርሻ

ሰ. አግባብነት ያለው የገበያ ክልል ውስጥ ያለው ስብስብ ወይም ክምችት

ሸ. ሌሎች ከዚህ ጋር ተያያዝነት ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ የዳሰሳ ጥናቱን መደረግ ይኖርበታል፡

20.3. የቅድመ ውህደት ዳሰሳ ጥናት ከሕዝብ ጥቅም አንጻር ሲታይ የሚከተሉት ነጥቦች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡-

ሀ. ውህደቱ ቢፈፀም የንግድ ዉድድሩን በመገደብ በህብረተሰቡ ላይ ከሚያደርሰዉ ተጽዕኖ ይልቅ ጠቀሜታዉ የሚያመዝን ሆኖ መገኘት አለመገኘቱን ፣

ለ. ውህደቱ ቢፈፀም የኢኮኖሚ ልማትን በማፋጠን ወይም ቴክኒካል እውቀትን በማስተላለፍ ወይም የንግድ ዕቃዎችን አመራረትና ስርጭትን ወይም የአገልግሎት አቅርቦትን በማሻሻል በኩል የጎላ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ስለመሆን አለመሆኑ፤

1. ውህደቱ የሚፈፀመዉ በመክሰር ላይ ያለ የንግድ ድርጅትን በመታደግ በኩል ያለዉ ድርሻ የጎላ ስለመሆ አለመሆኑ፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives

2. ውህደቱ ቢፈፀም በአገሪቱ በአነስተኛና ጥቃቃን ወይም በማይክሮ ወይም በአነስተኛ የንግድ ሥራ ዘርፍ ደረጃ የተቋቋሙትን ወይም የተሰማሩትን ነጋዴዎች ብቁ ወይም ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲገኙ ለማደረግ የሚረዳ ስለመሆን አለመሆኑ/የሚችሉበትን እድል የሚፈጥሩ ስለመሆ አለመሆኑ፡፤
3. ሌሎች ከቴክኖሎጂ ወይም ከብቃት ወይም ከተወዳዳሪነት አንፃር ጠቀሜታ ያላቸዉን ጉዳዮች

## 21. የውህደት ማስታወቂያ ተቃውሞ

21.1. ባለስልጣኑ በተዋሀጆች የቀረበውን ማስታወቂያ የተሟላ መሆኑን ማጣራት ካካሄደ በኋላ እንዳስፈላጊነቱ የተቃውሞ ጥሪ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በሚታተም ማስታወቂያ ያወጣል፡፡ ተቃውሞ ያለው አካል በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን በጽሁፍ በማድረግ በአመልካቹ በራሱ ወይም ህጋዊ ወኪል በአካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡

21.2. ባለስልጣኑ የሚያወጣው የተቃውሞ ማስታወቂያ ቀን፤ የአመልካቾች ስምና አድራሻ፤ ያመለከቱበት የውህደቱ ሁኔታ፤ የአመልካቾች የንግድ ስራ ቦታ፤ በምን ያህል ቀናት ተቃውሞ ማቅረብ እንደሚቻል፤ የባለስልጣኑ ስም እና ተቃውሞ የሚቀርብበት ቦታ እና ሌሎች ጉዳዮችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

21.3. የውህደት ዳይሬክቶሬት የተቃውሞ ማመልከቻ ካጣራ በኃላ የውሳኔ ሀሳቡን ለዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፡፡ የዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተርም የውሳኔ ሀሳቡን ለዋና ዳይሬክተሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያቀርባል፡፡ዋና ዳይሬክተሩም የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

21.4. የውህደት ተቃውሞ ማስታወቂያ ወጪ በውህደቱ አመልካች ድርጅቶች የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 22. የውህደት ማስታወቂያ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልገው ጊዜ

22.1. መካከለኛ የውህደት ዓይነት ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈለገው ጊዜ 15 የስራ ቀናት ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሲሆን ለተጨማሪ 10 የስራ ቀናት ሊራዘም ይችላል፡፡ጊዜው ሊራዘም የሚችለው በባለስልጣኑ ሲፈቀድ ነው፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives

22.2. ትልልቅ የውህደት ዓይነት ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልገው ጊዜ 30 የስራ ቀናት ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሲሆን ለተጨማሪ 15 የስራ ቀናት ሊራዘም ይችላል፡፡ ጊዜው ሊራዘም የሚችለው በባለስልጣኑ ሲፈቀድ ነው፡፡

## 23. ውሳኔ መስጠት

23.1. ከውደት ዳሰሳ ጥናት በኃላ ሊተላለፉ የሚችሉ ውሳኔዎች ውህደቱን መፍቀድ፤ መከልከል፤ ተያያዥ ግዴታዎችን በማስቀመጥ መፍቀድ፤ በልዩ ሁኔታ መፍቀድ ወይም የውህደት ፍቃድ መሰረዝ ሊሆን ይችላል፡፡

23.2. የሚተላለፉት ውሳኔዎች ይዘት የሚከተሉትን ሊይዝ ይችላል፤የአመልካቾች ስም፤የውሳኔውርዕስ፤ የማመልከቻው ይዘት፤የካፒታል መጠን፤የሼር ግብይት መጠን፤የውሳኔው ምክንያት፤የውሳኔው ማጠቃለያ፤የዋና ዳይሬክተሩ ወይም የተወካዩ ፊርማ ይሆናሉ፡፡

## 24. ውሳኔ ማሳወቂያ ጊዜ

24.1. ባለስልጣኑ ውሳኔውን ከወሰነበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቾች ወይም ለህጋዊ ወኪሎቻቸው በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

24.2. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 24.1. የተደነገገውቢኖርም ባለሰልጣኑ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች እንዳስፈላጊነቱ በድረ-ገጽ በኢሜል፤ በፖስታ፤ በፋክስና በደብዳቤ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

## 25. ስለ ይግባኝ

ባለስልጣኑ ውህደትን በተመለከተ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው አካል ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 26. የውህደት ማስታወቂያ ስለማቋረጥ

የውህደት አመልካቾች ባለስልጣን መ/ቤቱ በውህደቱ ፈቃድ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የውህደት ጥያቄው እንዲነሳ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

26.1. በዚህ መሰረት የሚቀርብ ጥያቄ በውህደት አመልካቾች በተናጠል ወይም በጋራ ሊቀርብ ይችላል፡፡

26.2. በአንቀጽ 26.1 መሰረት ከውህደት አመልካች አንደኛው ጥያቄውን ሲያቀርብ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሌላኛው ውህደት አመልካች/ቾች ያሳውቃል፡፡

26.3. አመልካቾች የውህደት ጥያቄያቸውን አቅርበው ለተከታታይ 3 ወር በባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያሟሉ የተጠየቁትን መረጃዎች እና ማስረጃዎች ካላቀረቡ እንዲሁም በሌሎች ህጋዊ ምክንያቶች የውህደት ጥያቄው ሊቋረጥ ይችላል፡፡

26.4. በባለስልጣን መ/ቤቱ ወይም በአመልካቾች የተቋረጠ ማመልከቻ በድጋሚ የውህደት ጥያቄ ማቅረብን የሚከለክል አይሆንም፡፡

26.5. የውህደት ማመልከቻው የተቋረጠው የውህደት ተጽእኖ ዳሰሳ ጥናት በተደረገ 6 ወር ጊዜ ውስጥ ከሆነ እና ማመልከቻው በድጋሚ ከቀረበ በቀድሞው ጥናት መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ግን ባለስልጣን መ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ድጋሚ የውህደት ተጽእኖ ዳሰሳ ጥናት ማድረግን አይከለክልም፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives
መዛግብት ቤት

## ክፍል ሰባት
## ድህረ ውህደት የዳሰሳ ጥናት እና ክትትል

27. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቀደም ሲል በሰጠው የውህደት ፈቃድ መነሻ ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎች ስለመፈጸማቸው ለመከታተል፤ ከውህደቱ ጋር ተያይዞ ጥቆማ ሲደርሰው እንዲሁም በራሱ ተነሳሽነት የድህረ ውህደት ዳሰሳዊ ጥናትና ክትትል ሊያደርግ ይችላል፡፡

28. የውህደት አመልካቾች የውህደት ፈቃድ ከተሰጣቸው በኋላ በገበያ ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ስለመሆኑ መረጃ ከተገኘ በአዋጁ አንቀጽ 36 መሰረት በምርመራ እንዲጣራ ለሚመለከተው ክፍል ውጤቱን እና መረጃ ይላካል፡፡

## ክፍል ስምንት
## እርምጃ ስለ መውሰድ

29. ባለስልጣን መ/ቤቱ ድህረ ውህደት ክትትል ወቅት የውህደት ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች፡
    - 29.1. የውህደት ፈቃድ ያገኘው በሀሰተኛ ወይም በተሳሳተ እና የተጭበረበረ ማስረጃ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
    - 29.2. ውህደቱ የተፈቀደው በቅድመ ሁኔታዎች ሆኖ ቅድመ ሁኔታዎቹን ያለመሟላቱ ሲያረጋገጥ የውህደት ፈቃዱን በአዋጁ አንቀጽ 13 መሰረት ሊሰርዝ ይችላል፡፡

30. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከላይ በአንቀጽ 29 (1 እና 2) መሰረት የወሰደውን እርምጃ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ማሳወቅ እና ተፈጻሚነታቸውን መከታተል አለበት፡፡

Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

31. **ስለማሻሻል**

የዚህ መመሪያ አውጪው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

32. **መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ……………… ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አቶ ያዕቆብ ያላ 08/07/2008 ዓ.ም

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትር

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት